# <u>ለመሪው የተዘጋጀ</u>

## <u>ጥናት አንድ (2ኛ ዮሐ 1-6)</u>

1. እውነት የሚለው ቃል በተለይ በዚህ ሥፍራ የሚያተኩረው ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በዩሐ 14:6 «እኔ መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ» ያለው ይመስላል::
2. ይህች በዚህ ስፍራ ስለ ተጠቀሰችው ሴት ሁለት አይነት አመለከከት አለ:: የመጀመሪያው ሐዋርያው በአገልግሎቱ ያገኛት አማኝ አድርጎ ማየት ሲሆን ሌላው ደግሞ በአከባበው የምትገኝ ቤ/ክ እንደሆነች ያምናሉ:: በእኔ አመለከከት ሁለተኛው ሃሳብ ከመልዕክቱ ሃሳብ ጋራ ይሄዳል ብዬ አምናለሁ::
3. በሁለቱ ሃሳቦች መሃል ትልቅ ልዩነት አለ:: የመጀመሪያው ከሴትየዋ ጥሩነት የተነሳ ሊደረግ የሚችል ሲሆን ሁለተኛው ግን እውነትን (ክርስቶስን) ከማወቅ የተነሳ በቤተሰብ መሃል ሊኖር የሚገባውን ፍቅር የሚያመለክት ነው::
4. እውነትና ፍቅር በተለይ በዚህ ክፍል ተጣምረው የምናይበት ምክንያት እውነት (ክርስቶስን) በውስጣችን ከመኖሩ የተነሳ በማለትም የሚወድበትን ምክንያት ይናገራል:: ስለዚህ እውነት በውስጤ አለ የሚል ፍቅርን የመለማመድ ግዴታ አለበት:: ይህም ሃሳብ በተለይ በቁጥር 6 ላይ በትዕዛዝ መልክ ሰፍሮ ይገኛል::
5. ዮሐንስ ደስ የተሰኘው አማኞች በእውነት ሲመላለሱ በማየቱ ነው:: እያንዳንዱ ሰው የራሱን ሃሳብ ይሰንዝር::
6. የትዕዛዝ ፍጻሜ ፍቅር እንደሆነ ቃሉ ስለሚናገርና ህግጋት ሁሉ በፍቅር እንደሚጠቃለሉ ስለሚናገር ተጨማሪ ህግ ሳይሆን የሚያስፈልገው በተሰጠው ህግ እንዲመላለሱ ማሳሰብና ማበረታት ነው የሚያስፈልገው::
7. በቁ5-6 የሰፈረልን ነገር ፍቅር በትዕዛዝና በማብራሪያ መልኩ ሲሆን ቁ1-2 ደግሞ ይህ ፍቅር በሐዋርያውና በሌሎቹም አማኞች ውስጥ በህይወታቸው በሥራ ሲገለጥ ነው::
8. በፍቅር መመላለስህ ክርስቶስ በውስጥህ ለመኖሩ አንዱ ማረጋገጫህ ነው::

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሁለት (2ኛ ዮሐ 7-13)

1. 2ኛ ዮሐ 1-6 ያለው ክፍል በእውነት ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ክፍል ማለትም ቁ7-13 ደግሞ በሀሰት ትምህርትና በሀሰተኞች ላይ በማተኮሩ ተቃራኒነታቸው ግልጽ ነው:: ወይም አንዱ እውነትን ማበረታቱና ሌላው ደግሞ ሐሰትን መቃወሙ::
2. ወደ ዓለም ወጥተዋል  ያለ የሚናገረው ከቤ/ክ ውስጥ ነው:: አማኞች  የመሰሉና  ያስመሰሉ ይመላለሱ የነበሩ በግ መሳይ ተኩላዎች ናቸው:: 1ዮሐ 2:19 ንና ሐዋ ሥራ 20፤30ን ተመልከት::
3. ስለነዚህ አሳቾች ይህ ክፍል የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች:- ሀ) ብዛት ያላቸው መሆኑን ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ መሆናቸውንና ሐ) ገና እንደሚመጡ ሳይሆን አሁን በአለም ውስጥ እንዳሉ ያሳየናል:: ይህንን ቁጥር ከይሁዳ ቁ4 ጋራ የሚያመሳስለው ሁለቱም እነዚህ አሳቾች ወደ አለም የገቡና በመከከላችን መሆናቸውን መናገራቸው ነው::
4. በዚህ ክፍል መሰረት የክርስቶስ ተቃዋሚ መለያ ሆኖ የቀረበው ነገር የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መምጣት አለመቀበል ነው:: እነዚህ አሳቾች ችላ ሊባሉ የማይገባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ:: አንደኛው የቁጥራቸው ብዛት ሲሆን ሁለተኛውና ዋነኛው የትምህርታቸው ይዘት ማለትም ክርስቶስ በሥጋ አልመጣም የሚለው የደህንነታችንን መሰረት ሁሉ የሚያፈርስ በመሆኑ ነው::
5. በሁለቱም ክፍሎች የምናገኘው ሃሳብ ሃሰተኛ ትምህርትን ማንኛውም ሰው ትልቅ ይሁን ትንሽ ይዞ ቢመጣልን በፊት ለፊት መቃወም ያለብን ነገር እንደሆነ ይጠቁሙናል::
6. ቁ8  ስክ ዛሬ ይዘነው የቆየነውን  ውነት የመተውና የመጣል አደጋ እንዳለ ያሳያል:: በቁ9 ላይ ደግሞ ወደኋላ የቀረን በማስመሰል በክርስትና አዲስ የማናውቀው ልምምድ ውስጥ የመግባት የመፈለግ አደጋ ሲሆን በቁ10-11 ያለው ደግሞ በራችንንና ልባችንን ለሁሉ ክፍት የማድረግ አደጋን ያሳዩናል::
7. ቁ10 ላይ የሰፈሩት ሀሳቦች ማለትም: ይህንን ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤ ሰላም አትበሉት፤ የሚቀበለው ሰው የክፉ ስራው ተባባሪ ይሆናል::» የሚለው ነው::
8. ግልጽ የሆነ የሀሰት ትምህርትን ሊያስተምር ወደ ቤታችን የሚመጣውን እንጂ ይህ ክፍል ሌሎችን ሰዎች አይጠቀልልም::
9. እታንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይግለጥ::